# የገቢ ከፍተኛ ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀትና ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ

**323/2013**

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አስተዳደር
ARCHIVE
Ministry of Transport

የካቲት 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የገቢ ከፍተኛ ጭነት / Bulk Shipment/ አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀት እና ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ

## መ ግ ቢ ያ

አገራችን ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት በማስመዝገብ ላይ ባለችው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እና ልማቱ በፈጠረዉ ከፍተኛ መነቃቃት ወደ አገር ዉስጥ ምናስገባዉ የገቢ ዕቃ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ በዓይነትም ሆነ በመጠን እየጨመረ መምጣቱ ይታወቃል፡፡ ይህን ከፍተኛ እድገት ተከትሎ በሁሉም ሊባል የሚችል በመፍትሄ ዙሪያ የሚደረገው እንቅስቃሴ ከንግድ እንቅስቃሴ ማደግ ጋር የተመጣጠነ ባለመሆኑ በሎጅስቲክስ አቅርቦትና አጠቃላይ በዕቃ አነሳስና የማጓጓዝ ሂደት ላይ ጉልህ ችግር ተከስቷል፡፡ ይህ ችግር የሎጅስቲክስ ጊዜ ማራዘምና የሎጅስቲክስ ወጪ ማናር ከሚያስከትለው ጉዳቶች በላይ በሀገር ገጽታ (Image) ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ በመሆኑም ይህ ችግር መቀጠል የለበትም፡፡ ሁሉም አካል ችግሩ እንዲቀጥል መፍቀድ አይኖርበትም፡፡

የሀገሪቱ ዋና ዋና ገቢ ዕቃዎች ነዳጅ ፣ ደረቅ ብትን ጭነት እና ጀነራል ካርጎ ሲሆን የሀገሪቱ የብትን ጭነት ደግሞ በዋናነት ማዳበሪያ፣ የእርዳታና የግዢ እህል፣ ሲሚንቶ፣ ስኳር እና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የድንጋይ ከሰል ሲሆን ከአገራችን ገቢ ዕቃዎች ውስጥ በክብደት በአማካይ 50% ያህል ነው፡፡ የከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipment) አስመጪዎች በዋነኛነት መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ናቸው፡፡

ይህ ጭነት በአንድ ጊዜ (lot) ከፍተኛ ክብደት የመጫን አቅም ባላቸው የጭነት አጓጓዥ መርከቦች (Bulk Carriers) የሚጓጓዝ ሲሆን በአብዛኛው በአንድ ጊዜ (lot) ከ25,000-30,000 ቶን አንዳንድ ጊዜም በአንድ ጊዜ 50,000 ቶንና ከዛ በላይም ይጓጓዛል፡፡ ጭነቱን የሚያጓጉዙት መርከቦች በወደብ ማሸጊያ (Berth) ተጠግተው ለመስተናገድ ከፍተኛ ጥልቀት (Draft) የሚጠይቁ ትላልቅ መርከቦች ናቸው፡፡ የጭነቱ የኦፕሬሽን ባህሪው መሬት ሳይራገፍ ከመርከብ በቀጥታ በተሽከርካሪዎች ላይ በመጫን (Direct Delivery Operation) የሚጓጓዝ ነው፡፡ በመሆኑ ጭነቱ ከመርከብ ተራግፎ በቀጥታ በተሽከርካሪዎች ላይ እንዲጫን

የሚደረግበት ሂደት እንዳይስተጓጎል ማድረግ ከተቻለ በወደብ ሊኖር የሚገባውን ተገቢ የመርከብ ቆይታ ጊዜ በመጠበቅ በወደብ የመርከብ ማሸጊያ መጣበብንና የወደብ መጨናነቅን ለመከላከል ይቻላል፡፡

ኦፕሬሽኑ በተፈለገው ተገቢ ጊዜ እንዳይከናወን ሂደቱን ሊያስተጓጉሉ የሚችሉ ሁኔታዎች የሚከሰቱበት አጋጣሚዎች እንዳሉ የሚታወቅ ሲሆን ከነዚህም መካከል በዋነኛነት የመርከቦች አመጣጥ ቅደም ተከተል፣ ከወደብ የማስተናገድ አቅም አኳያ ተገናዝቦ ዕቅድ ላይ ሳይመሠረት በተመሣሣይ ወይም በተቀራራቢ ጊዜ ውስጥ ወደ ወደብ ተደራርቦ መምጣት፣ በአገር ውስጥ የማከማቻ ሥፍራ / መጋዘን/ ዝግጅት ችግር ፣ የተሽከርካሪዎች አቅርቦት እጥረት፣ በወደብና በመርከብ መሣሪያና አሠራር ምክንያት የሚፈጠር የወደብ ዕቃን የማንሳት ውሱንነት የመሳሰሉ ችግሮች ሲያጋጥሙ የመርከብ የወደብ ላይ ቆይታ ጊዜ የሚራዘምበት እንዲሁም፤ ጭነቱ በወደብ ውስጥ መሬት ላይ እንዲራገፍ እና ወደ ወደብ መጋዘን ተጓጉዞ እንዲከማች የሚያስገድድ ሁኔታ የሚፈጠር ሲሆን ይህም አላስፈላጊ ወጪ እና ተያያዥ ችግሮችን ያስከትላል፡፡

የችግሮቹ ተፅዕኖ ከወጪ አንጻር ቢታይ የመርከብ የወደብ ላይ ቆይታ ጊዜ በመራዘሙ ምክንያት የሚፈጠር ክፍያ (Demurrage)፤ በወደብ ለመስተናገድ ተጨማሪ ኦፐሬሽን ውስጥ በመግባት ምክንያት (charges due to double operation) የሚፈጸም ክፍያ፤ ማለትም ጭነቱ በወደብ ውስጥ መሬት ላይ ከተራገፈ በኋላ ለሚሰጥ አገልግሎት /shore handling/ ተጨማሪ ወጪ ያስከትላል፤ ወደ ወደብ መጋዘን ከተጓጓዘ ደግሞ ከዚህ በላይ ለከፍተኛ የማከማቻ ተጨማሪ ወጪ የሚዳርግ ይሆናል፡፡

ችግሮቹ ከዚህም ባለፈ ለመርከብ ማሸጊያ (Berth) መጣበብና የወደብ መጨናነቅ፤ ኢኮኖሚያዊ የተሽከርካሪ አጠቃቀምን በማወክ የሚፈጠር የተሽከርካሪ እጥረት፣ ዕቃው በተፈለገው ወቅት ለተፈለገው ዓላማ በወቅቱ ያለመድረስ እና በግብይት ሥርዓት ላይ የሚፈጠር የዋጋ መናር ወዘተ የሚያስከትሉ በመሆኑ በአስመጪዎች፣ በወደብ፣ በላኪዎችና በኦፕሬተሮች መካከል አለመግባባት እና ከፍተኛ ቅሬታና ተያያዥ ችግሮችን አስከትሏል፡፡

በመሆኑም የሀገራችን የገቢ ዕቃዎች ንግድ ልማት ለመደገፍ መከናወን ካለባቸው ቁልፍ ተግባራት ውስጥ አንዱ የትራንዚት ወጪና ጊዜን ለመቀነስ የሚያስችል የትራንዚት ሥርዓት እና የገቢ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ በአጭር ጊዜ ለማጓጓዝ የሚያስችል

የአሠራር መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ ነው። ከዚህ አኳያ የአገሪቱ የገቢ ንግድ በሚፈለገው ደረጃ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱ የተረጋገጠ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ቀልጣፋ የወደብና የትራንዚት አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል እንዲሁም የገቢ ብትን ጭነት ብቻ ሳይሆን በአንድ ጊዜ (lot) ከፍተኛ መጠን ያላቸው የገቢ ጭነት ከምችት በባህር ወደብ እንዳይኖር እና ተቀናጅቶ እንዲገባ የሚያደርግ የአሠራር መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ የግድ ይላል።

በዚህ መሠረት ከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipment) የትራንዚት ሥርዓት የሚመራበትን ስታንዳርድ አሠራር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እና የሚመለከታቸው አካላት እስካሁን ተግባራዊ እያደረጉ የቆዩት ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የገቢ ንግድ ልማት መስኩ የታለመለትን ዓላማ ያሳካ ዘንድ የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነቶችና ግዴታዎች ለመወሰን በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 አንቀጽ 18 (ለ) ለሚኒስቴሩ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል።

ARCHIVE

# ክፍል አንድ - ጠቅላላ ድንጋጌ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ‹‹የገቢ ከፍተኛ ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀትእና ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. የቃላት ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1. **ከፍተኛ መጠን ጭነት** (Bulk Shipment) ፡- ማለት በአንድ ጊዜ ወይም በአንድ ኦፐሬሽን ክብደታቸው 5,000 ቶን እና ከዛ በላይ መጠን ያላቸው እንደ ድንጋይ ከሰል (Coal) ፤ ስኳር፤ ሲሚንቶ፤ ብረትና የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ሲሆን በተለይም በብትን በመርከብ ተጓጉዘው መሬት ላይ ሳይራገፉ በወደብ ላይ ታሽገው /Bagged/ በቀጥታ በመኪና ላይ በመጫን /Direct Delivery/ የሚጓጓዙትን እንደ ማዳበሪያ እና የእርዳታ እህል የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

2.2. **የዕቃ አስተላላፊነት እና መርከብ ውክልና፡-** ማለት በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕቃ ተቀባይን ወይም ዕቃ ላኪን በመወከል የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት፤ የወደብ ሥነ ሥርዓት እና ሌሎች ሥነ ሥርዓቶችን አስፈጽሞ የገቢ ወይም የወጪ ዕቃዎች በወደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ ማድረግ ሲሆን ዕቃን የማጓጓዝንና የማስረከብን ሥራ ይጨምራል፤

2.3. **ዕቃ አስተላላፊ፡-** ማለት በዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ. 37/1990 መሠረት የዕቃ አስተላላፊነት ለመሥራት የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

2.4. **የመርከብ ውክልና** ማለት የመርከብ ባለንብረትን፤ ተከራይን፤ ወይም ኦፐሬተርን በመወከል፤ መርከቡ የሚያጓጉዘውን ዕቃ ወይም መንገደኛ ማግኘትንና መመዝገብን፤ በባህር ወደብ ላይ እና በአገር ውስጥ ለመርከቦች

አገልግሎት መስጠትን፤እንዲሁም መሰል ተግባራት ማከናወንን ይጨምራል፡፡

2.5. **የመርከብ ወኪል፡-** ማለት በዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ. 37/1990 መሠረት የመርከብ ውክልና ለመሥራት የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

2.6. **የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፡-** ማለት በደንብ ቁ. 37/1990 በተወሰነው እና ሚኒስቴሩ ወደፊት በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሰረት በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ዉክልና፤ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት የንግድ ሥራ ላይ፣ እንዲሁም ሌሎች በዘርፉ የተመለከቱ የንግድ ሥራዎች ላይ ለመሰማራት የሚያበቃ የሙያ ብቃት ያላቸው ሠራተኞች እና የቢሮ አደረጃጀት መሟላቱን በማረጋገጥ በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የሚሰጥ ማስረጃ ነው፤

2.7. **የመጫን ፣የማራገፍ፣ የመቋጠር አገልግሎት** (Stevedoring and Bagging)፡- ማለት በመርከብ የመጣ ብትን ጭነት ከመርከብ መሬት ላይ ሳይራገፍ የማሸግ እና መኪና ላይ መጫን ፤ እንደዚሁም ከ "silo" በጆንያ በመቋጠር መኪና ላይ የመጫን አገልግሎት ነዉ፤

2.8. **ድርጅት** ማለት የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ሲሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 255/2004 የተቋቋመው የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው፤

2.9. **አዋጅ** ፡- ማለት የማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 ነው፤

2.10. **ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር፡-** ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

2.11. **ባለሥልጣን፡-** ማለት በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 መሠረት የተቋቋመው የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ነው፤

2.12. **ታሪፍ፡-** ማለት የዕቃ አስተላላፊ ወይም የመርከብ ወኪል ወይም በዚህ መመሪያ መሠረት ትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪነት የተሰማራ ኦፐሬተር ከዕቃ ላኪ ጋር ውል በገባበት ጊዜ የሚጠቀምበት የውል ሁኔታ ሆኖ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚጠይቀውን የአገልግሎት ክፍያ የሚጨምር ነው፤

2.13. ቻርተር /Charter/ ማድረግ፡- የመርከብ ድርጅቶች ከድርጅቶቻቸው መርከቦች በተጨማሪ የሌሎች የመርከብ ድርጅቶችን /ኩባንያዎችን/ መርከብ ተከራይተው የሚጠቀሙበት አሰራር ነው፡፡

2.14. ሰው፡- ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

## 3. የመመሪያዉ ዓላማ

መመሪያው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡

3.1. የአገሪቱን የወደብ አጠቃቀም ኢኮኖሚያዊነት በማረጋገጥ የገቢና ወጪ ንግድ ትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎት የወጪ እና የጊዜ ፍጆታ በዘላቂነት ለመቀነስ የሚያስችል ሥርዓት ለመተግበር፤

3.2. በባህር ወደብ ከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipment) አገልግሎት የሚሰጠውን ውስን የወደብ ፋሲሊቲ በአግባቡ በመጠቀም የመርከቦች መጠጊያ መጣበብን እና የወደብ መጨናነቅ ለማስወገድ የሚረዳ አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ፤

3.3. ከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipment) የጫኑ መርከቦች እና ጭነቶች በባህር ወደብ ለመቆየት ከተወሰነላቸዉ ጊዜ በላይ ሲቆ ሊከተል የሚችለዉን ተጨማሪ የወደብ ክፍያ (demurrage) እና ተደራራቢ የኦፕሬሽን ወጪ ለማስቀረት፤

3.4. ከባህር ወደብ ዕቃ በአፋጣኝ የማንሳት ዓቅም እና በአገር ውስጥ የመጋዘኖችን አጠቃቀም ብቃት በማሳደግ ብትን ጭነቶችን የሚያጓጉዙ የጭነት ተሽከርካሪዎች አቅርቦት እና የምልልስ ጊዜ ለማሳደግ፤

3.5. የከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipments) በታሰበው ጊዜ ለታሰበው ዓላማና አገልግሎት እንዲደርስ ለማድረግ

3.6. ከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipment) በተመለከተ በመንገድ ላይ የዕቃዎችን ደህንነት ለመጠበቅ ናቸው፡፡

## 4. አስፈጻሚ አካል

በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2፣ 8፣ 19 ሥር በተደነገገው መሠረት የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የገቢ ከፍተኛ ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀትእና ለመቆጣጠር የወጣውን ይህንን መመሪያ የማስፈጸም ስልጣን እና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

## 5. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈጻሚነት የሚኖረው ከውጭ ሀገር በባህር ተጓጉዞ ወደ ኢትዮጵያ በሚገባ በአንድ ጊዜ 5000 ቶን እና ከዚያ በላይ በሆነ ከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipment) ላይ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## መመሪያው የሚመለከታቸው አካላት ሃላፊነትና ተግባር

### 6. የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት

ይህንን መመሪያ በተመለከተ ባለስልጣኑ የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡

6.1. የከፍተኛ መጠን ጭነቶች (Bulk Shipments) የትራንዚት አገልግሎት አሰጣጥ የብቃት ስታንዳርድ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል አፈጻጸሙን ይከታተላል ፤ ይቆጣጠራል ፤እንዲሁም ስታንዳርዱን ያሻሽላል፡፡

6.2. የከፍተኛ መጠን ጭነቶች (Bulk Shipments) መረጃዎች የበጀት ዓመቱ በገባ በአስራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ከአስመጪዎች ይሰበስባል፡፡

6.3. ከላይ በተራ ቁ.6.2 የተሰበሰበውን መረጃ በመተንተን የበጀት ዓመቱን ገዢ የሆነ /Governing/ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ መርኃ ግብር /ዕቅድ/ ረቂቅ ያዘጋጃል፤ ከአስመጪዎች ፤ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪና አስፈጻሚ አካላት ጋር በሚደረግ ውይይት ዕቅዱ እንዲዳብር በማድረግ ያጸድቃል፡፡

6.4. በጸደቀው ዓመታዊ ገዢ የሆነ /Governing/ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ ብሄራዊ ዕቅድ መሠረት እንዲፈጸም ለአስመጪዎችና ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፡፡

6.5. ከላይ በተራ ቁ.6.3 መሠረት የጸደቀውን ገዢ የሆነ /Governing/ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ ብሄራዊ ዕቅድ እና ተጨማሪ የአፈጻጸም መርኃግብር አዘጋጅቶ በየሩብ ዓመቱ የመጀመሪያ አሥር ቀናት ውስጥ ለአስመጪዎችና ለሚመለከታቸው አካላት ይልካል፡፡

6.6. የከፍተኛ መጠን ጭነትን በተመለከተ በባህር ወደብ እና በሂደቱ የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን መለየት፣ እንዲሁም የወደብና የትራንዚት አገልግሎት በሚሻሻልበት ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ድርድር እና ምክክር በማድረግ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይፈታል፡፡

6.7. የአፈጻጸም ሂደት ደረጃዎች ግምገማ የሚደረግበት እና በወቅታዊ ጉዳዮችና በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊከናወኑ በሚገባቸው ጉዳዮች ዙሪያ

አስመጪዎችንና ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ የውይይት መድረክ ያዘጋጃል ፤ እንደአስፈላጊነቱ በትራንስፖርት ሚኒስቴር የሚጠራ የውይይት መድረክ ያስተባብራል፤ ይመራል።

6.8. በጸደቀዉ ዕቅድ እና መርሃ-ግብር መሠረት ከፍተኛ የብትን ጭነታቸዉን ለሚስገቡ አስመጪዎች እና የላቀ አገልግሎት ለሚሰጡ ዕቃ አስተላላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎች ተገቢዉን ግምገማ በማድረግ ዕዉቅና ይሰጣል።

6.9. የአስመጪዎች ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ የጸደቀውን ዕቅድ እና መርኃግብር ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ይከታተላል፤ ያለበቂ ምክንያት ይህንን መመሪያ በመጻረር የሚፈጽሙትን እና ከጸደቀ ዕቅድና መርኃግብር ውጪ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ ያስመጡ አስመጪዎችን ዝርዝር ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለሚኒስቴሩ አቅርቦ ያስወስናል፤ አፈጻጸሙን ተከታትሎ ሪፖርት ያቀርባል።

6.10. ከአስመጪዎች የሚደርሰዉን መረጃ መሠረት በማድረግ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ ግዢ አፈጻጸም ሂደት ላይ ጭነቱ የሚጓጓዝበት መርከብ ተገቢው የጉዞ ብቃት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል።

6.11. በባለስልጣኑ ዓቅም ሊፈቱ ያልቻሉ ችግሮች በሚመለከታቸው የበላይ አካላት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድባቸው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል።

6.12. የሀገሪቱ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ ከግዢ ጀምሮ ያለውን የሎጅስቲክስ ሰንሰለት ለመቆጣጠርና ለመከታተል እንዲቻልና በሀገር ደረጃ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ሊያስገኝ በሚችል የግዢ ተርም መጠቀምና በዚሁ መሰረት ለማከናወን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡

6.13. በብሄራዊ ደረጃ የተቀናጀ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሚረዱ አሠራሮችን ለመተግበር የሚያስችል ሃሳብ እና ጥናት እያዘጋጀ ከሚመለከታቸው አስመጪዎች፣ ተቆጣጣሪና አስፈጻሚ አካላት ጋር በመምከር እንዲፈጸሙ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር አቅርቦ ያስጸድቃል ፤ የጸደቀውን ጥናት አፈጻጸም ይከታተላል።

6.14. አስመጪዎች የባንክ ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት በባህር ወደብ የወደብ መጣበብ መኖርና አለመኖሩን ተለዋጭ ፕሮግራም መኖሩን ፤ አማራጭ ወደብ መኖሩን በማረጋገጥ መረጃ ይሰጣል፤

6.15. በእያንዳንዱ ኦፕሬሽን ሂደት ሀገሪቱን ለዲመሬጅ የዳረገ አካልን ተጠያቂ የሚያደርግ የውሳኔ ሃሳብና ሪፖርት ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

6.16. የዕቃ አስተላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎች የአገልግሎት አሰጣጥ ባለስልጣን መስሪያቤቱ ባዘጋጀዉ የብቃት ማረጋገጫ ስታንደርድ መሰረት አገልግሎት አሰጣጣቸዉን እና ታሪፋቸዉን ይቆጣጠራል ፤ ብቃታቸዉ ተረጋግጦ በመስኩ የተሠማሩ ድርጅቶችን ዝርዝር ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፤ ለንግድ ሚኒስቴር እና ለባህር ወደብ ባለሥልጣናት ያሳዉቃል ፡፡

## 7. የትራንስፖርት ባለስልጣን ተግባር እና ኃላፊነት

ይህንን መመሪያ በተመለከተ የትራንስፖርት ባለስልጣን የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡

7.1. ይህን መመሪያ በተመለከተ ከማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን በሚያገኘው ዓመታዊ ገዢ /Governing/ የሆነ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ ብሄራዊ ዕቅድ መሰረት ፕሮግራሙ ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ የተሽከርካሪ አቅርቦትን በተመለከተ ዝግጅት ያደርጋል ፤ ተከታትሎ ያስፈጽማል፡፡

7.2. የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን በሚያወጣው የዕቅድ መርኃግብር መሠረት አስመጪዎች የሚያስመጡትን ዓመታዊ እና የየሩብ ዓመት የገቢ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ ብሄራዊ ዕቅድ መሠረት በማድረግ የተሽከርካሪ ስምሪት እና የታሪፍ ሁኔታዎች ተከታትሎ የሚቆጣጠርበት አሠራር ዘርግቶ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

7.3. የገበያ መርህን ማዕከል ያደረገ የጭነት ታሪፍ አሠራር እንደተጠበቀ ሆኖ አላግባብ በሚደረግ የዋጋ መናር ወይም ያልተገባ ጥቅምን ታሳቢ በማድረግ የብትን ጭነት አመጣጥ ኦፕሬሽንን ፍሰት የሚያስተጓጉሉ የተሽከርካሪ አገልግሎት አሰጣጥ እክሎችን እየተከታተለ ተገቢ እርምጃ ይወስዳል፡፡

7.4. የትራንስፖርት ውሎችን ከአስመጪዎች በመቀበል የተሽከርካሪ አቅርቦትን ይከታተላል፤ በተሽከርካሪዎች ላይ የሚፈጠሩና ምልልስን የሚገቱ ሁኔታዎችን ይቆጣጠራል ፤ የአንጓገሮችን አሰራር ለመወሰን በወጣው አዋጅ

ቁጥር 547/99 መሰረትም የዲመሬጅ ህግን ተግባራዊ እንዲሆን ስርዓት ይዘረጋል፤ ለባለተሸከርካሪዎች ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡

7.5. የገቢ ከፍተኛ መጠን ጭነት (Bulk Shipments) ወደ አገር ዉስጥ የማጓጓዝ ሂደቱ የተቀላጠፈ እንዲሆን ለማስቻል በየብስ ትራንስፖርት ዙሪያ የሚከሰቱ ማነቆዎችን ለመፍታት ተገቢ የሆኑ መፍትሄዎችን ተግባራዊ ያደርጋል

## 8. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተግባር እና ኃላፊነት

ይህንን መመሪያ በተመለከተ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡

8.1. የገቢ ከፍተኛ መጠን ጭነትን /Bulk shipment/ በተመለከተ ከማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ከሚላክለት የዕቃ አስተላላፊዎች ዝርዝር ውጪ ሌሎች በዚህ አገልግሎት እንዳይሰማሩ ይቆጣጠራል፡፡

8.2. የገቢ ከፍተኛ መጠን ጭነትን /Bulk shipment/ የተመለከተ ዕለታዊ የወደብ እንቅስቃሴ /Port Position/ መረጃ ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ይሰጣል፡፡

8.3. ገቢ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ ከባህር ወደብ ጀምሮ በሚያልፍበት የትራንዚት ኮሪደር በሚገኙት ኬላዎች የመንገድ ላይ ስርቆት እንዳይፈጸም ተገቢዉን ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

8.4. የገቢ ከፍተኛ መጠን ጭነት ትራንዚትን በተመለከተ ከጉምሩክ አሰራር ጋር የተያያዙ ማነቆዎችን ይፈታል፡፡

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ARCHIVE
Ministry of Transport

## 9. ንግድ ሚኒስቴር ተግባር እና ኃላፊነት

ይህንን መመሪያ በተመለከተ ንግድ ሚኒስቴር የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል።

9.1. ከማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ብቁ የዕቃ አስተላላፊዎች ዝርዝር ሲደርሰው ለከፍተኛ መጠን ገቢ ጭነት /Bulk shipment/ አስመጪዎች እና ለሚመለከታቸዉ ሁሉ ያሳውቃል።

9.2. ከባለሥልጣኑ በሚደርሰዉ መረጃ መሠረት ብቃታቸዉ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመቀነሱ ሥራቸዉን በአግባቡ የማይወጡ ዕቃ አስተላላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎች የንግድ ሥራ ፍቃድን ይሠርዛል ለባሥልጣኑ እና ለሚመለከታቸዉ ሁሉ ያሳዉቃል፣

9.3. የገቢ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ ትራንዚት ሂደት ጋር የተያያዙ የንግድ ሥርዓት ማነቆዎችን ተከታትሎ ይፈታል።

## 10. የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ተግባር እና ኃላፊነት

ድርጅቱ በዕቃ አስተላላፊነት እና በመርከብ ውክልና አገልግሎት ሰጪነቱ የሚጠበቅበት ግዴታና ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ በተመለከተ የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል።

10.1. ድርጅቱ ከሌሎች የመርከብ ኩባንያዎች /ድርጅቶች/ መርከብ በመከራየት ወይም በ/Charter/ ብትን ጭነት ጫኝ መርከቦችን በሚጠቀምበት ወቅት የተከራያቸውን መርከቦች የጉዞ ብቃት ያረጋግጣል።

10.2. የብትን ጭነት የባህር ማጓጓዝን ኢኮኖሚያዊ ለማድረግ ድርጅቱ የራሱን መርከብ በመጠቀምም ሆነ ቻርተር በማድረግና በሌሎች መሰል ዘዴዎች በመጠቀም ለብትን ጭነት የባህር ላይ ማጓጓዝ አገልግሎት ይሰጣል።

## 11. የዕቃ አስተላላፊዎች ተግባር እና ኃላፊነት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ.37/1990 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ በተመለከተ ማናቸውም የዕቃ አስተላላፊ የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡

11.1. አግባብ ባላቸው ሕጎች፣ ደንቦችና በዚህ የገቢ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ የትራንዚት ሥርዓት መመሪያ እና ባለስልጣኑ በሚያወጣው ስታንዳርድ መሠረት ይሰራል፡፡

11.2. አስመጪውን በመወከል የወደብ ታሪፍና በትራንዚት ሂደቱ ውስጥ የሚኖሩ የሶስተኛ ወገን ታሪፎችን የመቆጣጠርና ተገቢነት የሌላቸው ወጪዎች ያስቀራል፡፡

11.3. ባለስልጣኑ በሚዘረጋው የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት መሰረት የስራ አፈጻጸሙን በተመለከተ ዕለታዊ መረጃ ለባለስልጣኑ ያቀርባል፡፡

11.4. ዕቃ አስተላላፊዉ በአሰራሩ ፤ በአድራሻው ፤ ከሌላ ሀገር ዕቃ አስተላላፊዎች ጋር የገባውን ውል እና በተለያዩ ጉዳዮች ለውጥ ሲያደርግ ይህንኑ ለውጥ በወቅቱ ለባለስልጣን መስሪያቤቱ ያሳውቃል፡፡

11.5. ለአስመጪው የተሟላ መረጃ የመስጠት እና አስመጪው በተሟላ መረጃ ላይ ተመስርቶ የአስመጪነት ሥራውን እንዲሰራ ይደግፋል፡፡

## 12. የመርከብ ወኪል ተግባር እና ኃላፊነት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ. 37/1990 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ በተመለከተ ማንኛውም የመርከብ ወኪል የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡

12.1. አግባብ ባላቸው ሕጎች፣ ደንቦችና በዚህ የገቢ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ የትራንዚት መመሪያና ባለስልጣኑ በሚያወጣው ስታንዳርድ መሠረት ይሰራል፡፡

12.2. አገልግሎት ለሚሰጠው የመርከብ ኩባንያ የወደብ ፕሮግራም የተሟላ እና ወቅታዊ መረጃን እንዲሁም የመረጃ ለውጦች ሲኖሩ ለባለስልጣን መ/ቤቱ ይሰጣል፡፡

## 14. የማስፈጸሚያ ስልት

ከዚህ መመሪያ ጋር በክፍል ሶስት አባሪ ሆኖ የተያያዘዉ የገበ. ከፍተኛ መጠን ጭነት ትራንዚት አገልግሎት ሥርዓት አፈጻጸም ስታንዳርድ የመመሪያዉ አካል በመሆን የማስፈጸሚያ ስልት ሆኖ ያገለግላል ::

## 15. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከዛሬ ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል::

አዲስ አበባ--------ቀን 2005 ዓ.ም

ድሪባ ኩማ
የትራንስፖርት ሚኒስትር

ARCHIVE

# ክፍል ሶስት

## የገቢ ከፍተኛ ጭነት /Bulk shipment/ አገባብን ለማቀናጀት የሚያስችል የአሰራር ስታንደርድ

**መግለጫ**

የከፍተኛ ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀት የወጣ መመሪያን ለማስፈጸም እና በመመሪያው ውስጥ ሃላፊነትና ተግባር የተሰጣቸው አካላት ኃላፊነቶቻቸውን በአግባቡ ማከናወናቸዉን ለመከታተልና አፈጻጸማቸውን ለመለካት እንዲያስችል ይህ ወጥ የሆነ ከፍተኛ ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀት የሚያስችል ሀገራዊ ስታንዳርድ ተዘጋጅቷል፡፡

ስታንዳርዱ ሲዘጋጅ በዋናነት መሰረት ያደረገዉ ከፍተኛ ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥን በብሄራዊ ደረጃ በማቀናጀት የትራንዚት ትራንስፖርት ጊዜ እና ወጪን ከመቀነስ አንጻር የተደረገ ጥናትን፣ በዚህ ደረጃ በጥናት የተገኘውን አማካኝ ውጤት መሰረት በማድረግ ፤ በስታንዳርዱ ላይ የዘርፉን ተዋናኝ አካላትን አስተያት በማካተት እና የፈጻሚ አካላትን ስምምነት በመዉሰድ ነዉ፡፡

በመሆኑም ስታንዳርዱ የስራው ሂደት የሚወስደውን ጊዜና የሚየስፈልገውን ቅድመ ሁኔታ እንዲሁም የተግባሩን ፈጻሚ አካል በግልጽ በማስቀመጥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ARCHIVE
Ministry of Transport

## የገቢ ከፍተኛ ጭነት /Bulk shipment/ አገባብን ለማቀናጀት የሚያስችል የአሰራር ስታንደርድ

| ተ.ቁ | ተግባራት (ሂደት) | የጊዜ ስታንደርድ | የሥራው ባለቤት |
|---|---|---|---|
| 1 | በበጀት ዓመቱ ለማስመጣት ያቀደውን ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ ዕቃ ዓይነት፣ መጠን እና የጊዜ መርኃግብርን የተመለከተ እንዲሁም ሌላ በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የሚጠየቀውን መረጃ አዘጋጅቶ ለባለስልጣኑ ያቀርባል፤ | የበጀት ዓመቱ በገባ በ 15 ቀናት ውስጥ | አስመጪዎች |
| 2 | ከላይ በተራ ቁ. 1. የተሰበሰበውን መረጃ በመተንተን የበጀት ዓመቱን ገዢ የሆነ /Governing/ ብሄራዊ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ መርኃግብር ዕቅድ ረቂቅ ያዘጋጃል፤ ከአስመጪዎችና ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪና አስፈጻሚ አካላት ጋር በሚደረግ ውይይት የጭነት አመጣጥ ፕሮግራም ያዘጋጃል። በተዘጋጀው ዓመታዊ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ ገዢ የሆነ /Governing/ ብሄራዊ ዕቅድ መሠረት እንዲፈጸም ለአስመጪዎችና ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል። | መረጃው በደረሰ በሰባት ቀናት ውስጥ | የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን |
| 3 | በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሰው የገቢ ዕቃዎች ገዢ የሆነ /Governing/ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ አመጣጥ ፕሮግራም መሰረት የተሽከርካሪ አቅርቦትን በተመለከተ አስቀድሞ ዝግጅት ያደርጋል ፤ ተከታትሎ ያስፈጽማል። በትራንስፖርት አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያላቸውን ጉዳዮች በመለየት የአጓጓዦችን አሰራር ለመወሰን በወጣው አዋጅ መሰረት በየጊዜው እየተከታተለ አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል። | ፕሮግራሙ ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ | ትራንስፖርት ባለስልጣን |

| ተ.ቁ | ተግባራት (ሂደት) | የጊዜ ስታንደርድ | የሥራው ባለቤት |
|---|---|---|---|
| 4. | ከላይ በተራ ቁጥር 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ኦፕሬሽን ወይም ጊዜ 5000 ቶንና ከዛ በላይ የሚያስገቡ አስመጪዎች የባንክ ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት የጭነቱን መረጃ ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ያሳውቃሉ፡፡ | ጭነት ወደብ ከመድረሱ አስቀድሞ ቢያንስ ከ45-60 ቀናት በፊት | አስመጪዎች |
| 5. | የወደብ ፕሮግራምና ተዛማጅ መረጃዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢውን መረጃ (ወደቡ ዝግጁ መሆኑን ፣ ተለዋጭ ጊዜ መኖሩን ፣ አማራጭ የትራንዚት ኮሪደር መኖሩን ፣ የወደብና የሌሎች የሎጅስቲክስ አቅርቦቶች መሟላታቸውን ወይም አለመሟላታቸውን) ለአስመጪው ይሰጣል፡፡ | ጥያቄው በቀረበ በ3 ቀናት ውስጥ | የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን |
| 6. | ጭነቱ የባህር ወደብ ከመድረሱ አስቀድሞ ቢያንስ 15 ቀናት በፊት አስመጪው የወከለውን ዕቃ አስተላላፊ ፣ ከባህር ወደብ ወደ መድረሻ ጣቢያው አጓጓዡን ፣ በሀገር ውስጥ ዕቃው የሚከማችበት የመጋዝን ዝርዝር ዝግጅትና የውል ስምምነት ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣንና ለትራንስፖርት ባለስልጣን ያቀርባል፡፡ | ጭነቱ የባህር ወደብ ከመድረሱ አስቀድሞ ከ15 ቀናት በፊት | አስመጪዎች |
| 7. | በተራ ቁጥር 6 የተገኘውን መረጃ ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች ይልካል፡፡ | መረጃው በደረሰው በሶስት ቀናት ውስጥ | የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን |
| 8. | መርከብ ወደ ማሽጊያ /Berth/ የማስጠጋትን ስራ፤ የወደብ ክሊራንስ የማስጨረስ ፣ ተሽከርካሪዎች ጭነቱን ለመጫን የሚያስፈልጋቸውን ፎርማሊቲዎች የማጠናቀቅ፤ የጭነት መጠን ልኬቱን የመከታተል ፣ ለጭነት የተዘጋጁና ወደብ የደረሱ ተሽከርካሪዎችን በወቅቱ የመጠቀም እና በአጠቃላይ ጭነት ከወደብ በተገቢው ጊዜ የማንሳት ስራ ያጠናቅቃል፡፡ | ዕቃው ወደብ በደረሰ ከ1-7 ቀናት ውስጥ | ዕቃ አስተላላፊ |

| ተ.ቁ | ተግባራት (ሂደት) | የጊዜ ስታንደርድ | የሥራው ባለቤት |
|---|---|---|---|
| 9. | በተራ ቁጥር 2 በተጠቀሰው ገገር /Governing/ ከፍተኛ መጠን ጭነት /Bulk shipment/ ፕሮግራም ቅደም ተከተል መሠረት የተሟላ የመርከብ እና የወደብ የማስተናገድ አገልግሎት መሰጠቱን ያረጋግጣል፡፡ | መርከቡ ወደብ በደረሰ ቢያንስ በሁለት ቀናት ውስጥ | የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን፣ የባህር ወደብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት |

Ministry of Transport ARCHIVE